በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስቅዱስ

አሐዱ አምላክ አሜን፡፡

# የሐዋርያው የቅዱስ ጳውሎስ መልዕክት ወደ ሮሜ ሰዎች


መምህር፡- ቀሲስ ሰሎሞን ሙሉጌታ

**E-mail:** kesisolomon4@gmail.com


***ቦታ፡-*** ቦሌ ደብረ ሳሌም መድኃኔዓለም ቤተ ክርስቲያን አዳራሽ

በየሳምንቱ ረቡዕ ምሽት ከ12፡30 – 1፡30

ኅዳር ፮ ቀን ፳፻፬ ዓ.ም.

# የሐዋርያው የቅዱስ ጳውሎስ መልዕክት - ምዕራፍ 4

- ቅዱስ ጳውሎስ ያለ እምነት ሕግን መፈጸም እንደማያጸድቅ ከገለጠልን በኋላ አብርሃምን በማንሳት በእምነት ስለሚገኘው ጽድቅ ገልጦልናል፡፡
- ቅዱስ ጳውሎስ አብርሃም የሁሉ አባት እንደሆነ በእግዚአብሔር በማመን ይሆንልን ዘንድ የተሰጠን ጽድቅ ለአይሁድም ለአሕዛብም ነው፡፡ የተገለጠው እምነትም ኢየሱስ ክርስቶስ አምላክ ወልደ አምላክ ነው ብሎ ማመን ነው፡፡
- በምዕራፉ የተገለጠው ሥራ ኢየሱስ ክርስቶስ አምላክ ወልደ አምላክ ነው ብሎ ሳያምኑ የሚሠራ ሥራ ነው፡፡
- 4፡1 በሥጋ የተባለው በሕግ በሆነው ሥራ ማለት ነው፡፡
- አይሁድ በሥጋ የአብርሃም ልጆች በመሆናቸው ተመክተው ነበር፡፡
- 4፡2 ለአብርሃም የጽድቁ መሠረት ሥራው ብቻ ቢሆን የሚያስመካው በሆነ ነበር፤ ነገር ግን አብርሃም በሥራው ብቻ የጸደቀ አይደለም፡፡ አብርሃም ለሰው ልጆች በእግዚአብሔር ይሆን ዘንድ በተገባላቸው ቃልኪዳን እኛ አሁን በኢየሱስ ክርስቶስ አምላክነት እንዳመንን ‹‹አብራምም በእግዚአብሔር አመነ፥ ጽድቅም ሆኖ ተቈጠረለት።›› *ዘፍጥ 15፡6* እንደተባለ አመነ፡፡
- 4፡3 በሁሉም መንገድ የጸጋው ባለቤቶች የሚያደርገን የሚያጸድቀንም መሠረት እምነት ነው፡፡

# የሐዋርያው የቅዱስ ጳውሎስ መልዕክት - ምዕራፍ 4

- 4፡4 ለሚሠራ ሰው ደመወዝ መብት እንጂ ስጦታ ወይም ማበረታቻ አይደለም፡፡ ነገር ግን የእግዚአብሔር ጸጋው ያስፈልገናል እንጂ ይህ ደመወዝ የሚያጸድቀን አይደለም፡፡
- 4፡5 ለማይሠራ የተባለው በገዛ ሥራዬ እጸድቃለሁ ብሎ ለማይመካ ለማይል ሰው ማለት ሲሆን
- ለሚያምን ሲል ወደርሱ ወዶ አምኖ የሚቀርበውን ኃጢአተኛ በሚያጸድቅ በእግዚአብሔር ምሕረት ለሚታመን ማለት ነው፡፡
- እምነቱ ሲል ኢየሱስ ክርስቶስ አምላክ ወልደ አምላክ ነው የሚል በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነት ያለው አንድ ብቻ የሆነ ማለቱ ነው፡፡
- 4፡6 ዳዊት በእርሱ በተሠራው ሥራ ሳይሆን በቸርነቱ ያደርገው ዘንድ እግዚአብሔር የገባውን ቃልኪዳን አምኖ ተቀብሎታል፡፡
- ዳዊት ራሱ ታላቅ በደልን ያደረገ ቢሆንም ከእግዚአብሔር ዘንድ ይቅርታን ተቀብሏል፡፡
- 4፡7-8 በመዝ 31(32)፡1-2 ዓመፃቸው ወደፍርድ ሳያስቀርባቸው የተሰረየላቸው ኃጢአታቸውም በኢየሱስ ክርስቶስ ደም የተከደነላቸው በማለት ኃጢአቱን ሳይቆጥርበት ያጻደቀውን ዳዊትን አንስቶታል፡፡
- 4፡9 ይህ ይቅርታ የጠቀማቸው እነማን ናቸው? አይሁድ ወይስ አሕዛብ? የአብርሃም እምነቱ ጽድቅ ሆኖ ተቆጠረለት በማለት የእግዚአብሔር ምሕረት መሠረቱ እምነታችን እንደሆነ ገለጠ፡፡

# የሐዋርያው የቅዱስ ጳውሎስ መልዕክት - ምዕራፍ 4

- 4፡10 አብርሃም ይህ በዘፍ 15፡6 የተገለጠው ከተነገረ በኋላ ቢያንስ ለአሥራ አምስት ዓመታት አልተገረዘም ነበር፡፡ የጸደቀውም ሳይገረዝ ነበር፡፡ ታዲያ በኋላ ስለምን ተገረዘ?
- 4፡11-12 የተገረዘው የጽድቅ ስጦታ ማኅተም በርሱ የታተመ ይሆንለት ዘንድ ነው፡፡
- መገረዝ ምልክት ብቻ ሳይሆን በእምነታችን የሆነው ጽድቅ ማረጋገጫ ነው፡፡ መገረዝ ሞትና ሕይወት (ጥምቀት) ነው፡፡
- አብርሃም የሚያምኑት ሁሉ የአይሁድም የአሕዛብም - የተገረዙትም ያልተገረዙትም ነገር ግን የእምነ ቱን ፍለጋ ለሚከተሉ - ያለሥራ የሆነ እምነት ሙት ነውና ሥራውንም ለሚሠሩ ሁሉ አባት ነው፡፡
- 4፡13 የተስፋ ቃል የተባለው ለአብርሃምና ለዘሩ የተገቡለትን የተለያዩ ቃሊኪዳኖች የሚመለከት ነው፡፡ የሁሉ አባት ይሆን ዘንድ ቃል የተገባለት ነውና፡፡
- የሙሴ ሕግ የተሰጠው ከአብርሃም ብዙ ዘመናት ካለፉ በኋላ ነውና ለአብርሃም የሆነው በፊደል ሕግ አይደለም፡፡ አብርሃም ቃልኪዳኑ የተደረገለት በፊደል ሕግ ወይም በሕግ ሥራ ሳይሆን በእምነት በሆነው ጽድቅ ነው፡፡
- 4፡14 ወራሽነት ከሕግ ለሆኑት ከሆነ ወይም ሕግን መጠበቅ ብቻ ሰውን የሚያጸድቀው ከሆነ ማመን ከንቱ ነው ወይም አይጠቅምም ወደሚል ክህደት ያደርሳል፡፡

# የሐዋርያው የቅዱስ ጳውሎስ መልዕክት - ምዕራፍ 4

- ይህም ክህደት እምነትን እንጸድቅበት ዘንድ የሰጠንን የእግዚአብሔርን ዓላማ ማስወገድና በእምነት ይደረግልን ዘንድ የተገናውን ቃልኪዳን መናቅ ወይም መተው ነው፡፡
- 4፡15 ሕግ የሚጥሱትን ሁሉ ለመቀጣት አሳልፎ ይሰጣቸዋል፤ ማንም ሕግን ፈጽሞ አልጠበቀውምና ሁሉም የሚቀጡ ሆኑ፡፡
- ሕግ ባይኖር ሕግ ተላላፊነት አይታወቅም ለመተላለፍ መጣጣርም አይገኝም ነበር፡፡ ያለሕግ በደለኞች ነበርን በሕግ ደግሞ በደለኞችና ሕግንም ተላላፊዎች ነን፡፡
- 4፡16-25 ለአብርሃምና ለዘሩ የተገባው ቃል ኪዳን የተገኘው በእምነት ነው በእምነትም የጸጋው ስጦታ በነጻ ተሰጥቶናል፡፡ ይህም በሕግ በሆነ ጽድቅ ቢሆን ባልተረጋገጠልን ነበር፤ ሕግን ፈጽሞ የጠበቀው ማንም የለምና፡፡
- ሁሉም ጽድቁን በኢየሱስ ክርስቶስ ባለው እምነት ይፈጽማል፡፡
- ለዘሩ ሁሉ ሲል *__በዘፍጥ 17፡5__* ‹‹ነገር ግን ስምህ አብርሃም ይሆናል ለብዙ አሕዛብ አባት አድርጌሃለሁና…›› እንደተባለ በሕግ ከሆኑት የአብርሃም ልጆች ከአይሁድ ወይም የአብርሃም ልጆች ከሆኑት ከአሕዛብ ብሎ ሁሉን ማንሳቱ ነው፡፡
- ለሙታን ሕይወት በሚሰጥ ብሎ አብርሃም ለሙታን ሕይወትን በሚሰጥ በእርጅና ላሉት ለርሱና ለሳራም ሳይቀር አዲስ ሕይወትን በሚያድል በመለኮታዊው አምላክ ማመኑን ተናገረ፡፡
- የሌለውንም ቢሆን እግዚአብሔር አንስቶ በፊቱ ሊያደርገው ይችላልና እንዳለው አድርጎ አመነ፡፡

# የሐዋርያው የቅዱስ ጳውሎስ መልዕክት - ምዕራፍ 4

- የአብርሃም ዘሩ በዚያ ዘመን አልነበረም እግዚአብሔር ግን ጌታ ባሪያውን እንዳች ነገርን እንዲያደርግ እንደሚያዘው፣ ብርሃንን ባልነበረበት ጊዜ ብርሃን ይሁን ብሎ ሲፈጥረው እንደሆነ ሕይወትን ያዛልና ዘርህ ብሎ ስለወደፊቱ ተናገረ።
- አብርሃምና ሳራ ቢያረጁም እግዚአብሔር ዘርን ይሰጠው ዘንድ የገባለትን ቃል ኪዳን አመነ። *ዘፍጥ 15፡5…*
- አብርሃም በሥጋ ቢደክምም በራሱም ሆነ በሳራ በኩል ቃልኪዳኑ እንዳይፈጸም ለማድረግ የሚገጥመውን አካላዊ መሰናክል ሳይመለከት ለእግዚአብሔር ክብር እየሰጠ እግዚአብሔር ቃሉን እንደሚፈጽም በማመን በእምነቱ ጠነከረ።
- ይህም እምነቱ ጽድቅ ሆኖ ተቆጠረለት። ይህም የሆነው በሌላ ምክንያት ሳይሆን በእግዚአብሔር በማመኑ ሁላችን መረዳት ያስፈልገናል።
- በመጨረሻም እስከዚህ ድረስ ለማስረዳት የሄደበትን ለማጠቃለል ከሙታን ተለይቶ የተነሳውን ጌታችንን ኢየሱስ ክርስቶስን ባስነሳውም አንዲት ፈቃዱ ብናምን ይህ የሆነው እርሱ ስለበደላችን ተላልፎ የተሰጠልን መሆኑን እንረዳለን፤ በሞቱ ሞታችንን ሽሮ ኃጢአታችንን ደምስሶልናልና።
- በጥምቀት ከርሱ ጋር ሞተን አዲስ ፍጥረት ሆነን በትንሣኤው ከብረን እንነሳለን።

# ወስብሐት ለእግዚአብሔር።

For your queries or questions E-mail:
kesisolomon4@gmail.com

To get all the lessons, surf :
www.zeorthodox.org